## የአካለ ስንኩልነት ትርጉም

- የሕይወትን አንድ ወይም በርካታ እንቅስቃቄዎች የሚገታ የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳት ነው::
- የዚህን መሠል የጉዳት የሕይወት ታሪክ ወይም
- ይህን መሠል ጉዳት አለበት ተብሎ በህብረተሰቡ መወሠድ ነው::

### ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አባባሎች አንዱን ቢባሉ ምን ይሠማዎታል:

«የአዕምሮ ዘገምተኛ የሆኑ ሰዎች እዚህ እንዲኖሩ አንፈልግም:: ማን ሊንከባከባቸው ይችላል? የእነሱ እዚህ መኖር ለጐረቤቱ ሠላም ጥሩ አይሆንም»፣ ወይም

«የቤት ኪራይ መክፈል መቻልህን እንዴት እርግጠኛ መሆን እችላለሁ?»

«ቤቱን ላከራይህ ፈቃደኛ ነኝ:: ሆኖም ግን የኢንሹራንስ ክፍያዬ ሊጨምር ይችላል::» ወይም

«ለቤት እንስሳት ቦታ የለንም:: ይህ ደግሞ አንተን የሚመራውን ውሻ ያካትታል::» ወይም

«የሕክምና መረጃህን ማየት እፈልጋለሁ::» ወይም

«ዊልቸርህ ምንጣፉን ሊጐዳ ይችላል:: የእሳት አደጋ ቢነሳ ከዚህ መውጣት አትችልም::»

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን አባባሎች አካለ ስንኩላን የቤት አገልግሎት እንዳያገኙ የሚያደርጉ መድሎዎች ሲሆኑ፤ እነዚህም በዲሲ የሰብአዊ መብቶች ሕግና የቤት ባለቤትነት ደንብ የተከለከሉ ናቸው::

**መብቴ ተጥሷል ብለው የሚያስቡ ከሆነ የሰብአዊ መብቶች ጽ/ቤትን ያነጋግሩ:: የስልክ ቁ. (202) 727-4559 ወይም www.OHR.dc.gov**

የሚከተሉትን መረጃዎች ለመስጠት እባክዎን ይዘጋጁ

1. ስሞትን እና አድራሻዎትን መጥቀስ አይዘንጉ::
2. በአቤቱታ የሚያቀርቡበትን ግለሠብ ስምና አድራሻ
3. ሥለመብት ረገጣው የሚገልጽ አጭር ማብራሪያ
4. የመብት ረገጣው የተፈፀመበት ቀን



## ስለ እኩል መብት የተሰጠ መግለጫ

እ.ኤ.አ. በ1977 በወጣው የዲ.ሲ የሰብአዊ መብቶች ሕግ እንዲሁም በተሻሻለው የዲ.ሲ. ይፋዊ ሕግ አንቀጽ 2-1401.01 መሠረት የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የዘር፣ የቀለም፣ የሐይማኖት፣ የብሔር፣ የፆታ፣ የዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የመልክ፣ የወሲብ ዝንባሌ፣ የቤተሰብ ደረጃ፣ የቤተሰብ ኃላፊነት፣ የትምህርት ደረጃ፣ የፖለቲካ፣ የአካል ጉዳተኝነት፣ የገቢ ወይም የመኖሪያ እና የንግድ ቦታ መድልዎ አያደርግም:: በተጨማሪ ሕጉ የወሲብ ጥቃትን እንደፆታ መድሎዎ በመቁጠር ድርጊቱን ይቃወማል፣ ይከለክላልም:: ይህን ሕግ መጣስ ያስቀጣል:: ግዛቱ ሕጉን በማያከብሩ ነዋሪዎች ላይ አስፈላጊውን የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ይወስዳል::

የሰብአዊ መብቶች ጽ/ቤት በአሜሪካ የቤቶች እና የከተማ ልማት መምሪያ ሕጋዊ እውቅና የተሰጠው አካል ነው:: በዚህ ሕጋዊ እውቅና መሠረት ጽ/ቤቱ በቤት አሰጣጥ ላይ የሚደረጉ መድልዎችን ተከታትሎ በድርጊቶቹ ላይ በፌደራል ሕግ መሠረት ክስ ይመሰርታል::

**እኩል ቤት የማግኘት መብት ድንጋጌ መድሎዎችን በሰባት ከለላ ባላቸው ክፍሎች ይከለክላል:**

እኩል ቤት የማግኘት መብት (42 ዩ.ኤስ.ሲ 3601፣ እ.ኤ.አ. በ1968 የታወጀው የሲቪል መብቶች ሕግ አንቀጽ 8 እንዲሁም እ.ኤ.አ. በ1988 የተሻሻለው የቤቶች አስተዳደር ሕግ) ዘርን፣ ቀለምን፣ ብሔርን፣ ሐይማኖትን፣ ፆታን፣ አካለ ስንኩልነትን፣ የቤተሠብ ደረጃን (ማለትም ከ18 ዓመት በታች የሆኑና ከወላጆቻቸው ወይም ከሕጋዊ ሞግዚቶቻቸው ጋር የሚኖሩ ልጆችን፣ እርጉዝ ሴቶችን እንዲሁም ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆችን የሚያስተዳድሩ ዜጐችን ጨምሮ) በመመርኮዝ በቤቶች ሽያጭ፣ ኪራይ ወይም ግንባታ ወቅት የሚደረጉ መድሎዎችን ይከለክላል::

እ.ኤ.አ. በ1977 የተሻሻለው የዲ.ሲ. ሰብአዊ መብቶች ሕግ የፌደራል የቤቶች አስተዳደር ሕግን ይተካል:: በተጨማሪም ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ጉዳዮች የሕግ ከለላ ይሰጣል::

- ዕድሜ
- የጋብቻ/የቤተሰብ ሁኔታ
- ተክለ ሰውነት
- የመኖሪያ/የንግድ ቦታ
- የወሲብ ዝንባሌ
- የቤተሠብ ኃላፊነት
- የፖለቲካ አቋም
- የትምህርት ደረጃ
- የገቢ ምንጭ
- ጾታን ማንጸባረቅ ወይም አገላለጽ

**ከዚህ ሕግ የማይካተት የቤት ዓይነት:**

ሕጉ በመንፈሳዊ ድርጅቶች በሚንቀሳቀሱ የንግድ ባልሆኑ ቤቶች እንዲሁም ለአባላቶች መኖሪያነት ብቻ በሚያገለግሉ የግል ክለቦች ላይ ተፈፃሚነት የለውም::

የአሜሪካ የቤቶችና የከተማ ልማት መምሪያ ይህ በራሪ ወረቀት እንዲዘጋጅና እንዲታተም የገንዘብ አስተዋጽኦ አድርጓል::

## በአካለ ስንኩልነት ምክንያት የሚደረግ የቤት መድሎ ሕጋዊ አይደለም!





# ቤት የማግኘት መብትዎን ይወቁና ይጠብቁ

### የሰብአዊ መብቶች ዲ.ሲ. ጽ/ቤት

441 4th Street N.W., Suite 570N
ወይም
3220 Pennsylvania Avenue S.E.
Washington, D.C.
(202) 727-4559

## ተዘውትረው የሚጠየቁ ጥያቄዎች:

**ጥያቄ** - አንድ አከራይ «የቤት እንስሳትን» የሚመለከት መመሪያ የእንስሳትን አገልግሎት የሚፈልግ የአካል ጉዳተኛ አላከራይም ማለት ይችላል?

**መልስ** - አይችልም:: አንድ አከራይ የቤት እንስሳት መመሪያ ሊኖረው እና እርሱንም ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል:: ሆኖም ግን መሪ ውሻ ወይም አገልግሎት የሚሠጥ እንሰሳ እንደቤት እንሰሳ ተደርጐ ሊወሰድ አይችልም:: ምክንያቱም የዚህ እንሰሳ አገልግሎት የአካል ጉዳተኛውን መርዳት ነው::

**ጥያቄ** - አንድ አከራይ ተከራይ ቤቱን ሲለቅ በቤቱ ላይ ማሻሻያ እንዲያደርግ ቢፈቅድ ክፍሉን ለመለወጥ ወይም ወደ ቀድሞው ሁኔታ ለመመለስ ተጨማሪ የኪራይ ክፍያ ወይም የዋስትና ገንዘብ ሊጠይቅ ይችላል?

**መልስ** - አይችልም:: የኪራይ ክፍያ ወይም የዋስትና ተቀማጭ ገንዘብን መጨመር ከሕግ አንፃር አግባብ አይደለም:: ምክንያቱም ይህ ሁኔታ አካል ጉዳተኞችን  ጨምሮ በተለየ ሁኔታ የሕግ ከለላ በተሠጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም::

**ጥያቄ** - አንድ የኤችአይቪ/ኤድስ በሽተኛ የሕግ ከለላ አለው?

**መልስ** - አዎ አለው:: አንድ ኤችአይቪ ያለበት ግለሠብ ወይም የኤድስ በሽተኛ በሰብአዊ መብቶች ሕግ መሠረት የሕግ ከለላ አለው::

አከራይ አካለ ስንኩል ተከራይን አካለ ስንኩልነቱን የሚያሳይ መረጃ አካለ ስንኩልነቱም ከቤት ጥያቄው ጋር የተያያዘ መሆኑን ከሕክምና ባለሙያ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል::

## የሚከሠቱ መድሎዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

መኖሪያ ቤቱ ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች አገልግሎት ለመስጠት ምቹ ሆኖ ሳለ ሕጐችን፣ ፖሊሲዎችን እና የአገልግሎት መመሪያዎችን በመጣስ ቤቱ ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት እንዳይሠጥ ማድረግ::

### ምሣሌ:

አከራዮች በቤቱ ውስጥ በተመቻቸ ሁኔታ እንዳይኖሩ የሚያግድዎትን ሁኔታዎች ለማስቀረት ለአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች በሕግ እና በፖሊሲያቸው ላይ ማሻሻያ ሊያደርጉ ይገባል:: ቤቶ ውስጥ በመግባት እርዳታ ሊሰጥዎ ለሚችል ጓደኛዎ ተጨማሪ የቤት ቁልፍ ቢያስፈልግዎ አከራዩን ቁልፍ ሊይዙ የሚገባቸው ተከራዮች ብቻ ናቸው የሚለው ሕግ መቀየር ይኖርበታል::

በእሳት አደጋ ጊዜ የሚጮህ የአደጋ ማስጠንቀቂያ ደውል መስማት የማይችሉ ከሆነ አከራዩ ሕዝብ ሊያየው በሚችል ቦታ የሚታዩ የአደጋ ማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ማኖር ይኖርበታል:: የሚፈልጉትን የቤት ዓይነት እና የመገልገያ ቁሳቁሶች ግልጽ እና አጠር ባለ መልኩ ያስረዱ::

ለአካል ጉዳተኞች በተከራየ የመኖሪያ ቤት ላይ ዜጐቹን በሚመጥን እና በሚስማማ ሁኔታ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎችን ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆን::

### የተካተቱ ምሣሌ

- መግቢያ በሮችን ማስፋት
- የበር ጉበኖችን ዝቅ ማድረግ
- የአካለ ስንኩል የደረጃ መወጣጫ ድጋፍ
- በመታጠቢያ ክፍሎች ውስጥ የመደገፊያ ብረቶች መትከል

እኩል የሆነ የቤት አገልግሎት ሕግ ለአዕምሮ ዘገምተኞች፣ የአዕምሮ ሕመም እንዲሁም የመስማት እና የማየት ችግር ላለባቸው፣ ለኤድስ በሽተኞች፣ ምርኩዝ ወይም ዊልቸር ወይም የአገልግሎት ሰጪ እንሰሳት እና የሞግዚት አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸው ዜጐች የሕግ ከለላ ይሠጣል::

## በ1973 የተደነገገው የእደሳ አንቀጽ 504

አንቀጽ 504 የፌዴራል እርዳታ የሚያገኙ አዲስ ግንባታዎችን የሕዝብ ቤቶችን ወይም እርዳታ የሚያገኙ አምስት ወይም ከዛ በላይ ቁጥር ያላቸውን መኖሪያዎች ለሚገነቡ ከሐምሌ 1988 ወዲህ የሚገነቡትን እቅዳቸውን በሚመለከት ምን እንደሚጠበቅባቸው ያመለክታል: የሚገልጸውም: ከመቶው የተወሰነውን እጅ ሙሉ ለሙሉ የአካለ ስንኩልና ላላቸው ግለሰቦች (5%) ተመቺ እንዲሆን እና የእይታ ስንኩልና እና ወይም የመስማት ስንኩልና (2%) በተጨማሪም ተገቢ የሆኑ ለውጦችና ትብብሮች የመጠየቅ እና የመቀበል መብትን ያካትታል::

